የሰ/መ/ቁ.184388

መጋቢት 29/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ በዳዳ ኤጀርሳ

ተጠሪ፡ አቶ ቦከና ጉርሙ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ይቅረብልኝ አቤቱታን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቀ/318798 ላይ መስከረም 27/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአሁን አመልካች የቀረበለትን "ጊዜው ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ላቅርብ" የማስፈቀጃ ጥያቄን አስመልክቶ በቂ ምክንያት አልቀረበበትም በማለት ውድቅ ያደረገበት ትዕዛዝ "መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው" በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የማስፈቀጃ ጥያቄውን ያቀረቡት ቀደም ሲል ስራ ላይ በነበረው ህግ መሰረት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ሶስት ወር ሲሆን ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 216/2011 መሰረት ጊዜው ወደ ሁለት ወር ዝቅ ስለመደረጉ አላውቅም ነበር የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ምክንያቱ በቂ አይደለም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 05/2012 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎ ተፈፅሟል ያሉትም መሰረታዊ የህግ ስህተተ ጠቅሰው በዚሁ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በገጠር የምኖር አርሶ አደር በመሆኔ እና የክልል ህጎጋት እንኳንስ በገጠር በከተማም ተደራሽ ባለመሆናቸው አዲሱ ህግ ስለመውጣቱ

አላውቅም፤ የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜም ያለፈው በዚሁ ምክንያት ስለመሆኑ ገልጩ እያለ በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል ምክንያት የማስፈቀጃ አቤቱታዬ ውድቅ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ ትዕዛዙ ተሽሮ የሰበር አቤቱታዬ ቀርቦ እንዲታይ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተምርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በተሻሻለው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀፅ 27(2) መሰረት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 60(ስድሳ) ቀናት ውስጥ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ ከመደንገጉ ውጭ ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ቀርቦ ሊታይ ስለሚቻልበት ሁኔታ አዋጁ የደነገገው ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል እስከ አሁን ድርስ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ ወጥቶ ተግባራዊ የተደረገ ልዩ የሰበር ሰሚ ችሎት የሥነ ሥርዓት ህግ ባለመኖሩ እየተሰራበት ያለው በመደበኛው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ነው፡፡

እስከ አሁን ስራ ላይ ባለው የ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መሰረት ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ/የሰበር አቤቱታ/ ቀርቦ እንዲታይለት አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው ከአቤቱታው ጋር ጊዜው ሊያልፈ የቻለበትን ምክንያት የሚገልፁ ማስረጃዎችን ማቅረብ ያለበት መሆኑን እና ማስረጃዎቹም ይግባኙ/የሰበር አቤቱታው/ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልቀረበበትን ምክንያት የሚገልፁ እና ውሳኔም እንዲሰጥበት በቂ ሆነው መገኘት ያለባቸው ለመሆኑ በቁጥር 325(2) ደንግጓል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈባቸው አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜውን ያሻሻለው ህግ መውጣቱን ባለማወቃቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ እንግዲህ አንድ ህግ ተፈፃሚ የሚሆነው በሀገሪቱ ባለው የህግ ማውጫ/ማሳወቂያ ስርዓት መሰረት ከወጣበት ወይም በልዩ ሁኔታ ተፈፃሚ እንዲሆን ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እንጂ እያንዳንዱ ዜጋ ህጉ ስለመውጣቱ ካወቀበት ጊዜ አይደለም፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ምክንያታዊ ዜጋ በሀገሩ ውስጥ የሚወጡ ህጎችን ያውቃል ተብሎ ግምት የሚወሰድ በመሆኑ ህግን ያለማወቅ ይቅርታ የሚያሰጥ አይደለም፡፡ እናም ህግ መውጣቱን አላውቅም ነበር የሚለው ጉዳይ መከራከሪያ ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡት ምክንያት በቂ አይደለም ብሎ ውድቅ በማድረጉ የፈፀመው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቀ/318798 ላይ መስከረም 27/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካችን "ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ላቅርብ" ጥያቄን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ